ውድ የFCPS ማህበረሰብ ፡-

የመምህር-መር የርቀት ትምህርቱን ለመጀመር ሁለተኛውን ሙከራችንን ብናደርግም በBlackboard Learn 24-7 ለመጠቀም አስቸጋሪ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ለሁሉም ሰው የሚያናድድ እና ቅር የሚያሰኝ ነው፡፡ ተማሪዎቻችን እና አስተማሪያችን ለርቀት ትምህርት አስተማማኝ የሆነ ስርዓት እንደሚያስፈልጋቸው እናውቃለን፡፡ ስለሆነም Blackboard Learn 24-7 ን ለፊት ለፊት የመማሪያ ዘዴነት ከመጠቀም እንቆጠባለን። አስተማሪዎችን እና ተማሪዎችን የትምህርት መርጃዎችን እና ድጋፎችን ለማግኘት በ Blackboard Learn 24-7 መጠቀማቸውን ይቀጥላሉ ፡፡

በትምህርት ቤቱ ቦርድ ድጋፍና አቅጣጫ መሰረት ለ 189,000 ተማሪዎች የርቀት ትምህርት ዕቅዳችንን ለማሻሻል ተጨማሪ እርምጃዎችን እየወሰድኩ ነው ፡፡

በመጀመሪያ የርቀት ትምህርት ስርጭትን መሚመለከት አጠቃላይ ግምገማ እየጀመርኩ ነው። በቴክኖሎጂው እና የበይነመረብ ደህንነት/cybersecurity ልምድ ያለውን የህግ ድርጅት Hunton Andrews Kurth LLP ቀጥረናል። የርቀት ትምህርታችንን በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ለመቀጠል ከድርጅቱ ሪፖርት እንጠብቃለን ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በሦስት የሥራ ሊቀመንበሮች በጋራ የሚመራ የዋናው ተቆጣጣሪ የቴክኖሎጂ አማካሪ ምክር ቤት ከBobbie Kilberg, President and CEO of the Northern Virginia Technology Council; Andrew Ko, Managing Director of Global Education በ Amazon Web Services እና Amy Gilliland የGeneral Dynamics IT ፕሬዚደንት ጋር እያቋቋምኩ ነው።

ይህ ምክር ቤት መጀመሪያ ማንኛውንም አይነት የርቀት ትምህርት ችግሮች ለመፍታት የሚረዳ መመሪያ ይሰጣል። እንዲሁም የ K-12 ትምህርትን ለማሻሻል ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ይሰጣል። ምክር ቤቱ ቴክኖሎጂ እና የመሰረተልማትን በሚመለከት ምርጥ ተሞክሮዎችን ፣ የርቀት ትምህርትን የሚያሻስሉ አዳዲስ ሶፍትዌሮችን በሚመለከት እና ለተማሪዎች እና ለአስተማሪዎች የሚሆኑ ዘመኑ የፈጠራቸውን አዳዲስ ተክኖሎጂዎችን በሚመለከት ያማክራል። ምክር ቤቱ ከ K-12 አካባቢ ጋር የሚተገበሩ ስኬታማ የግሉ ዘርፍ ልምዶችንም ይመረምራል፡፡ FCPS ለተማሪዎ እና ሰራተኞቹ ዘላቂ ፣ ቀልጣፋ ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና የተገናኘ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር ግብ እንዳስቀመጠ እኔም ለዚህ ጉዳይ የእነሱን መመሪያ እጠብቃለሁ፡፡ የጋራ ሊቀመንበሮቻችን እነዚህን ጉዳዮች በተፋጠነ ሁኔታ ለመፍታት ያለውን አጣዳፊነትን ይገነዘባሉ ፡፡

አስገራሚ መምህራኖቻችን ፣ በት/ቤት የሚሰሩት የቴክኖሎጂ ባለሞያዎች እና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እንደ Google Classroom ባሉ ቴክኖሎጂዎች የተቀላጠፈ ትምህርት ለመስጠት ቀድሞ የተቀረጹ ቪዲዮዎች ፣ የመማር ጥቅሎች/እሽጎች ፣ ኢ-መጽሐፍት እና ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው የዲጂታል ግባቶችን ለተማሪዎች የፈጠራ ትምህርታዊ ዕድሎችን ማቅረባቸውን ይቀጥላሉ ፡፡ ተማሪዎችን በቻናል 21 ፣ 25 እና 99 ላይ ወደ መርሃግብሩ ይመራሉ። ደብዳቤ በመላክ ይሁን ፣ ድምጽን ከፍ አድርጎ በማንበብ ፣ ወይም ለተማሪዎች በመደወል መምህሮቻችን ግድ እንዳላቸው ያሳዩ ሲሆን እነዚህ ግንኙነቶች ይቀጥላሉ።

እንዲሁም ትምህርት ቤቶቻችን በBlackboard Learn 24/7 መጠቀም እያቆሙ እያለ ለተማሪዎቻችን የ“ፊት ለፊት” ትምህርት እንሰጣለን ፡፡ ት/ቤቶች ደህንነቱ በተጠበቀ Blackboard Collaborate Ultra link ወይም በሌላ አማራጭ መንገዶች አማካይነት የርቀት ትምህርት ለመስጠት ይዘጋጃሉ። ስለ በርቀት የመማር ዕድሎች እና ስለሚጠቀሙበት መድረክ መምህራን በሚቀጥሉት በርካታ ቀናት ውስጥ ተማሪዎችን ያነጋግራሉ።

ነገ እና ትምህርት ቤቶቻችን ስለመምህር-መር ትምህርት ያላቸውን እቅድ እስኪያሳውቁ ድረስ አስተማሪዎቻችን የፊት ለፊት ትምህርት አይሰጡም። ከዚህ ይልቅ መምህራኖቻችን በሌሎች መገልገያዎች በመጠቀም የመማር እድሎችን ማቅረባቸውን ይቀጥላሉ ፡፡

ምንም እንኳን የርቀት ትምህርት ጅማሬው እንደታሰበው ባይሆንም እስካሁን ድረስ ትምህርቱ ለመስጠት ለረዥም ሰአት ጠንክረው ለሰሩ መምህራን እና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች እጅግ በጣም አመሰኛለሁ።

በዚህ በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ውስጥ ላደረጉት ድጋፍ እና ትዕግስት እናመሰግናለን።

ከልብ:-

Scott Brabrand ዋናው ሃላፊ
Fairfax County የህዝብ ትምህርት